ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ግንቦት 29 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**ወያኔ ለጦሩ የመደለያ ማዕረግ መስጠት ጀመረ፣ ማዕረግ እና ሽልማት አሰጣጡ የዘር ሀረግን ማዕከል ያደረገ መሆኑም ተጋለጠ፣ ሁለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ከስራ ተባረሩ፣ የአሜሪካ ሬዲዮ ዘጋቢን ጨምሮ አምስት ዘብጥያ ወረዱ** »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

ከፍኖተ-ዴሞክራሲ የኢ.ትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝረዝር ያንብቡ ....................................

የጠባቡ ወያኔ ቡድን መሪዎች ስልጣን እንለቃለን እያሉ ባዶ ፕሮፓጋንዳ እየነዙና ህዝብን ለማታለል እየተሩሩዋጡ ባለበት በአሁኑ ወቅት የቡድናቸው መመሪያ ተቀባይ አድርገው ያስቀሩትን ሰራዊት በተለያዩ ምክንያቶች እያመሱት ስለመሆኑ ባለፉት ዘገባዎቻችን አጋልጠን ነበር

በታመኑ የመከላከያ ውስጥ አዋቂዎች ዘገባ ደቡብ ምስራቅ ዕዝ የተባለው የወያኔ የጦር ክፍል ውስጥ ሰሞኑን በተደረገው የማዕረግ አሳጣጥ ለወያኔ ቅርበት ያላቸውንና የዘር ሀረጋቸው እየተመረጠ ከምክትል መቶ አለቃ እስከ ሌተናል ኮሎኔል ድረስ ማዕረግተኞች እና ከተራ ወታደር እስከ ሀምሳ አለቃ ድረስ እንደዚሁ በተመሳሳይ መልኩ አንዳንድ ደረጃ ከፍ የተደረገላቸው መሆኑን አስረድተዋል

ይህ ከሐረር የደረሰን ዘገባ ወያኔዎቹ ከ7 ዓመታት በላይ ያገለገሉና በረሀ ለበረሀ ሲንከራተቱ የነበሩትን ነባር የሰራዊቱን አባላት አሳማኝነት የሌላቸውን የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን በመፍጠር ከስራ ያባረሩዋቸው ከመሆኑ ጋር እና ከሌሎች ተዛማጅ ችግሮች ጋር በተያያዘ ሰራዊቱ ማኩረፉን ጠብ መንጃ አምላኪው ወያኔ በድንጋጤ ተዘፍቆ የሚገኝ መሆኑን በመጥቀስ ሰራዊቱም ታጥቆት የነበረው ጠብ መንጃ የራሱን መብት ሳያስከብርለት ይቀራል ብሎ በእርግጠኝነት የመዋረጃውን ቀን በመጥቀስ የተናገረ ባይኖርም ግምቱን ጠቅሶ ወያኔን እኩይ ድርጊት ከወዲሁ ጠንቅቆ መረዳት ተገቢ ነው በማለት የገመተና የተናገረ በርካታ ነበር ምን ያደርጋል ሰሚ ጠፋ … ደጋግመን ያልነውና የፈራነውም ደረሰ .. ..

በሰራዊቱ ኩርፊያ እና ማልጎምጎም በስጋት ባህር የሚዋኘው ወያኔ ለወያኔ ቡድናዊ መመሪያ ተቀባይነታቸው አቻ ያልተገኘላቸውንና ለጄኔራል መኮንኖቹ ቅርበት ያላቸው መኮንኖች እና ባለ ሌላ ማዕረግተኞች የማዕረግ እድገት የተሰጣቸው ሲሆን ለአንዳንዶቹም ከማዕረግ እድገቱ በተጨማሪ የገንዘብና የቁሳቁስ ሽልማት እንደተሰጣቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ባለፈው ሳምንት ግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ. ም በሀረር ከተማ በምስራቅ ዕዝ ዋና መምሪያ ግቢ ውስጥ በተደረገው የማታለያና መደለያ የማዕረግ እድገት ላይ ተገኝቶ ሽልማትና እድገቱን የሠጠው የእዙ ዋና አዛዥ የወያኔ ሜ/ጀ/ል አብርሀ ወ/ማሪያም ሲሆን ባደረገው ንግግር «አኩራፊ የሆኑ ጥቂት መኮንኖች ሊፈጥሩ የነበሩት ችግር በቀላሉ በመንግስታችን ጥንካሬ ሊከሽፍ የቻለ ሲሆን ፤ እናንተም የዚህን ቡድን ሰንሰለት ለመበጣጠስ ያደረጋችሁት አስተዋፅኦ ቀላል ባለመሆኑ ለዚህ ድካማችሁ የዛሬውን ሽልማት እና የማዕረግ እድገት ሊሰጣችሁ ችሎዋል» ሲል ገልፆዋል::

እንደ ጄኔራሉ ገለጻ ከሆነ በዚህ ሰሞን ሽልማት እና የማዕረግ እድገቱ የተሰጣቸው መኮንኖች እና ባሌላ ማዕረግተኞች ለወያኔ ስርዓት ከፍተኛ ቅርበት ስላላቸው እንጂ በጦርነት ወይም በስራ ላይ ባሳዩት እንቅስቃሴ እንዳልሆነ ባደረገው ንግግር ላይ እራሱ አጋልጦዋል::

የወያኔ ቡድን ከተቃዋሚ ጋር ስትደራደሩ ተገኝታችሁዋል ፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመለካከት ይዛችሁዋል እያለና የተለያዩ ምክንያቶችን እየሰጠ ከሰራዊቱ ከማባረሩም በላይ ለሰራዊቱ መብት ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ የነበሩትን የጦሩ አባላት ከየጦሩ ክፍል እየለቀመ በማሰር ተግባር ተጠምዶዋል

በአሁኑ ወቅት ሰራዊቱ ከማኩረፉም በላይ አልፎ አልፎ ቁጣውን መግለፅ በመጀመሩ የተደናገጠው ወያኔ የሰራዊቱን ኩርፊያ እና ቁጣ ለማብረድ ሲባል ለወያኔ ቅርበት ያላቸውና በስለላ ሰራዊቱን ለሚያምሱት መኮንኖች እና ለበታች ሹሞች ሽልማት እና የማዕረግ እድገት እንዲሰጣቸው ከመሆኑም ባሻገር ቁልፍ ቁልፍ የተባሉ የሰራዊቱ ክፍሎችንም በበላይነት እንዲመሩ መደረጉን ይኸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

በሱማሊያ ምድር በወያኔ መሪዎች ፍላጎት ሳይወዱ በግድ ገብተው በሺህዎች የሚቆጠሩትን ወገኖቻቸውን አስጨርሰው የተመለሱትን የሰራዊቱ አባሎች ያለምንም ጡረታ ከስራ የመባረራቸውን መርዶ ያየው የሰማውና የተረዳው ቀሪው የጦሩ አባል ነግ በኔ ነው በሚል ቁጣውን ገልፆ እንደነበር ያስታወሰው ዘገባ ይህንኑ ተከትሎ የወያኔ መሪዎች እና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው እነ ሳሞራ የኑስ የተለያዩ ምክንያት ለጥፈው በድጋሚ በቀሪ አባሎች ላይም ምንጠራ ማድረጋቸውን ዘገባው አብራርቶዋል::

በበረሀ ከሰባት ዓመታት በላይ እየተንከራተቱ የነበሩትን ነባር የሰራዊቱ አባሎች ከ2 ወር በፊት በተደረገ የማሰናበቻ ስነ ስርዓት ላይ ለእያንዳንዱ ተሰናባች የጦሩ አባል ከ9 እስከ 12 ሺህ ብር ብቻ እየሰጡ ያባረሩዋቸው ከመሆኑም በላይ በየሄዱበት ክልል ችግር እንዳይፈጥሩ በሚል እና ለመቆጣጠር እንዲያመች ልዩ መታወቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ያስታወሰው ዘገባ በአሁኑ ሰዓት በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ጉም ጉምታ እየሰፋና እያደገ በመሄዱ ከማዕረግ መደለያው በተጨማሪ አዳዲስ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ የገጠር ወጣቶችን መልምለው በማሰልጠን ላይ መሆናቸውን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በሁርሶ፤በጦላይ፤በብላቴ ፤በአድዋ፤ በሽሬ፤ በደብረዘይት፤እና በሌሎችም በተለያዩ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖች ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩ አዲስ ምልምል ወታደሮችን አስገብተው እያሰለጠኑ ሲሆን ምልምል ወታደሮቹ ስልጠናቸውን አጠናቀው በየጦሩ ክፍል እየተመደቡ እንደሆነም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ነባሩ የሰራዊቱ አባሎች በወያኔ ጄኔራሎች እና ሹማምንቶች እርምጃ በመበሳጨት በተለይ ይህ የማእረግ እድገት ከመሰጠቱ 15 ቀናት ቀደም ብሎ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ የሰራዊቱ አባሎች ከነሙሉ ትጥቃቸው እየከዱ መሆናቸውንም የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ ባሉ ከፍተኛ መኮንኖች መሀከል ሳይቀር ልዩነቱ ከመስፋቱም በላይ እርስ በርስ በቡጢ እስከመደባደብ ድረስ ተደርሶ እንደነበር ያስታወሰው ዘገባ በአሁኑ ሰዓትም የወያኔ ባለስልጣናት የሰራዊቱን ቀልብ ለመያዝ ሙከራ እያደረጉ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ካለመቻላቸውም በተጨማሪ

የአንድ ወገን የበላይነት ቀድሞ ከነበረው በላይ ነግሶ ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ችግሩ እየሰፋና እያደገ በመሄዱ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሎዋል::

ሰሞኑን የዚሁ የሰራዊቱን መፍለስ እና ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር መቀላቀልን ተከትሎ መለስ ዜናዊ እና በረከት ስምኦን የፀረ ሽብርተኝነት ህግ በሚል ረቂቅ ለምክር ቤት ያቀረቡ ሲሆን በዚህ ህግ ላይ ትጥቅ አንግቦ ወያኔን የታገለ ፤ ለመብት ለነጻነቱ መስዋዕት ሊሆን የፈለገን ፤ሀገሪቱን ለመታደግ በትጥቅ ትግል የሚታገሉትን ኃይሎች ሽብርተኛ በሚል ተቀፅላ ስም ለጥፈውና አስለጥፈው ማጨብጨብ በሚወደው ፓርላማቸው ውስጥ ስያሜ አሰጥተው በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ትግላቸው እንዲኮላሽ ለማድረግ ሲሉ አዲስ ስልት የነደፉ መሆኑንም ዘገባው አክሎ ገልጾዋል::

በቅርቡ የመፈንቅለ መንግስት ሊያደርጉ ሲሉ ነበር በማለት መግለጫ በነበረከት ስምኦን ተሰጥቶባቸው ከየአቅጣጫው እየተለቀሙ የታሰሩት መኮንኖችን መልሰው የመንግስት ባለስልጣናትን ለመግደል እና የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለማውደም ሲያሴሩ ተደርሶባቸዋል በማለት ቀይረው ለይምሰል ፍርድ ቤት አቅርበው ነበር ለማለት ያህል ብቻ በ10 ደቂቃ ውስጥ እያደረሱ የመለሱዋቸው ከመሆኑም ሌላ ብ/ጄ/ል ተፈራ እና ብ/ጄ/ል አሳምነው ጨምሮ 7 የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸውን መኮንኖች እጃቸውን በካቴና ሰንሰለት አይናቸውን በጥቁር ጨርቅ አስረው ችሎት እያቀረቡ እንደመለሱዋቸው ምንጮቹ ገልፀዋል::

ከማዕከላዊ ምርመራ ሽራ በለበሱ ሽፍን መኪኖች እያመላለሱ የይስሙላ ፍርድ ቤታቸው ሲያቀርቡዋቸው እንደነበር የተመለከቱ የአይን ምስክሮች በተለይ የቡድኑ መሪ ናቸው የተባሉትን ብ/ጄ/ል ተፈራንና አሳምነውን ጨምሮ 7 ኮሎኔሎችን ማንም ሰው እንዳያያቸው ተደርጎ እጃቸው እና አይናቸው ታስሮ ችሎት የቀረቡ ቢሆንም ዳኛው የወያኔ ምልምል በመሆኑ ፋይሉን እንኳዋን ሳያይ የ14 ቀን ቀጠሮ ሰጥቶ ማሰናበቱን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ለሰራዊቱ መብት መከበር የተሙዋገቱ የጦር መኮንኖችን የተለያዩ ሰበቦች እና ምክንያቶች እየሰጡ በማደን ለእስራት እየዳረጉ ያሉት እነ መለስ ዜናዊ በ1997 ዓ.ም.ከሀገር አቀፍ ምርጫ ጋር በተያያዘ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድጋፍ አድርጋችሁዋል በሚል አስረዋቸው የነበሩትን መኮንኖች እስከ አሁን ድረስ ያለምንም ጥያቄ በእስር ላይ እንዳሉና በቅርቡ ገና ወደ ጦር ፍርድ ቤት ሊያቀርቡዋቸው ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም በሰራዊቱ ውስጥ በአንድ ብሔር ላይ ያነጣጠረ ምንጠራ እየተካሄደ በመሆኑ ከሌላው ጊዜ በተለየ የወያኔን ቡድን ሊከፋፍለው እንደቻለና ከእንግዲህም ሊጠገን እንደማይችል ውስጥ አዋቂዎቹ እየገለፁ ይገኛሉ::

ከበረሀ ጀምሮ ሲታገሉ ነበር የተባሉ የብአዴን መኮንኖች እና ተከታዮቻቸውን በተናጠል እያደኑ ለእስር ፤ ለእንግልት እና ለስደት እየዳረጉ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት በተለይ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ የጥቃት ዘመቻ መክፈታቸው የብአዴንን ካድሬዎች ጭምር ያስከፉ በመሆኑ በወያኔ መሀከል እጅግ የከፋ የሰፋና ሊጠገን የማይችል ክፍተት እንደተፈጠረም የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ::

በተመሳሳይ ዜና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባደረበት ውስጣዊ ፍርሀት የተነሳ በአሁኑ ሰዓት አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃ ላይ ባሉት ወታደሮች ባለ መተማመኑ በምስጢር በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ልዩ ኮማንዶ እያሰለጠነ መሆኑን ምንጮች ገለፁ::

ከአንድ ሻለቃ በላይ የሚሆኑት እነዚሁ ልዩ ኮማንዶ ሰልጣኝ ምልምል ወታደሮች በውጭ ሀገር ሰዎች እየሰለጠኑ ከመሆኑም በላይ ስለነዚህ ሰልጣኞች የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች እንደማያውቁ እና በምስጢር በመለስ ዜናዊና በጄ/ል ሳሞራ የኑስ ብቻ ትዕዛዝ የተመለመሉና ወደፊትም በሁለቱ ባለስልጣናት ብቻ የሚታዘዙ መሆናቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል:: ከ6 ወር በፊትም የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ምልምሎች ናቸው በተባሉ አዲስ ወታደሮች የውስጥ ጥበቃ ሲደረግ የቆየ ቢሆንም አሁን ደግሞ በፍርሀት ዙሪያ ጥበቃ ላይ ያሉት ወታደሮች በሙሉ ሊቀየሩ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ለብዙ ዓመታት የከፍተኛ በፍርድ ቤት በዳኛነት ሲያገለግሉ የነበሩትን ሁለት ዳኞች የተለያየ ሰንካላ ምክንያት ሰጥተው ከስራ ያባረሩዋቸው ሲሆን በቀጣይም ይኸው እርምጃ እንደሚቀጥል የደረሰን ዘገባ ገለፆዋል:: አቶ ዘመድ አትርሳው እና አቶ ሳሙኤል የተባሉት ሁለቱ ግለሰቦች ሰሞኑን የተለያየ ሰንካላ ምክንያት ተለጥፎባቸው ከስራ ገበታቸው ላይ የተባረሩ ከመሆኑም በላይ አዲስ የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው ወደፊት በህግ ሊጠየቁ ይችላል በሚል ስጋት በብዙዎች ዘንድ እንዳሳደረም ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ የተደረገው የዳኞቹ ምንጠራ ዘመቻ ቀስ በቀስ አሁንም ሌሎች የአማራ ብሔር ተወላጅ ዳኞች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ እያቆበቆቡ መሆኑንም ዘገባው ገልፆ በአሁኑ ሰዓት ከመቼውም ጊዜ በላይ በወያኔ ውስጥ የአንድ ወገን የበላይነት ነግሶ እንዲወጣ ለማድረግ በረከት ስምኦንና መለስ ዜናዊ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

የወያኔ ቡድን መሪዎች መለስ ዜናዊና አሽከሩ በረከት ስምኦን በብአዴን አባሎች ላይ ያነጣጠሩት የምንጠራ ዘመቻ ለጊዜው ጋብ ያለ መስሎ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ቀስ በቀስ እንደገና ውስጥ ውስጡን እያንሰራራ መሆኑን የገለፀው ዘገባ ባለፈው ሳምንት ውስጥም የአሜሪካ ሬዲዮ ዘጋቢን ጨምሮ የታሰሩት ሰዎች የዘመቻው አንዱ አካል እንደሆነም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

ረቡዕ ግንቦት 19 ቀን 2001 ዓ.ም. ከዋናው ግምሩክ ግቢ ውስጥ በደህንነት ተለቅመው የታሰሩት የአሜሪካ ሬዲዮ ዘጋቢ መለስካቸው አምሀን ጨምሮ ሌሎች አምስት ሰዎች እራሳቸው ወያኔዎች ፈቅደው እና አፅድቀው የሰጡዋቸውን በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡትን የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ለመረከብ ዋናው የጉምሩክ መስሪያ ቤት የተገኙ ቢሆንም እነ በረከት ስምኦን በደህንነቶቻቸው አፍሰው ለእስር የዳረጉዋቸው መሆኑንና ፍርድ ቤት ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. አቅርቦ የ14 ቀን ቀጠሮ እንደተሰጠባቸውም ይኸው ዘገባ ገልጾዋል::

ወያኔ በተለይ በአማራ ተወላጆች ላይ የጀመረውን የመንጥር ዘመቻ አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ከምንም ጋር ግንኙነት የሌላቸውን የአማራ ብሄር ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ በርካታ ነጋዴዎች፤ምሁራኖች፤እና የተለያዩ ግለሰቦች የዚሁ የመንጥር ዘመቻው ሰለባ እየሆኑ እንደሆነም ዘገባው አስረድቶዋል::